DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

የካቲት (February) 17, 2017

ውድ የዲሲፒኤስ (DCPS) ማኅበረሰብ፣

በዲሲፒኤስ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS)፣ ተማሪዎች ሁሉ፣ መምህራን እና ሠራተኞች የድህንነት ዋስትና ያላቸው እንዲሆኑ ማራጋገጠ ተቀዳሚ ተግባራችን ሲሆን፣ ትምህርት ቤት ለመማር እና ለማስተማር ተግባር አመቺነት ያለው መሆን አለበት። ይህንንም ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንዴት እንደምናካሂድ እንድትገነዘቡት ለማድረግ፣ ትምህርት ቤታችንን በየጊዜው እንዴት ጠብቀን እንደምን ይዘው እና ንጽሕናውንም እኔት አድርገን እንደምንከባከበው፣ እንዲሁም ተባዮችን እንዴት አድርገን እንደምንቆጣጠር ጥቂት መረጃዎችን ላካፍላችሁ እወዳለሁ። በተጨማሪም በርከት ያሉ መረጃዎችን በበለጠ ዝርዝር በ it[https://dcps.dc. gov/page/health-and-wellness](https://dcps.dc.gov/page/health-and-wellness). እንድታነቡ አበረታታለሁ።

ዓመቱን በሙሉ፣ ዲሲፒኤስ፣ ችግሩ ከመከሰቱ በፊት ቀደም ብሎ ከጠቅላላ አገልግሎት መምሪያ (Department of General Services (DGS)) ጋር ተባዮችን ለመከላከል እና ሊያስከትሉ የሚችሉትንም ማናቸውንም ሥጋት (የአይጥ ዝርያዎችን፣ ተባዮችን፣ ወዘተ) ከትምህርት ቤቶች ሁሉ ለመከላከል፣ በመሥራት ላይ ይገኛል። ዲሲፒኤስ እና የጠቅላላ አገልግሎቶች መምሪያ (DGS)፣ ሊፈጠሩ የሚችሉ የተባይ ምንጮችን ፈልጎ ለማግኘት፣ የሚፈለፈሉበትን እና ወደ ትምህርት ቤቶችም የሚዛመቱባቸውን ማናቸውንም መንገዶች ለመቆጣጠር፣ ሕንጻ ነክ መግቢያ ቀዳዳ የሆኑ ለተባዮች አስተዋጽዖ ሊያበረክቱ ይችላሉ የሚባሉ መንገዶችን ሁሉ ለመዝጋት፣ አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ ፀረ ተባይ (exterminators) አገልግሎቶች እና ተቆጣጣሪዎችን ጭምር ለማምጣት፣ ከትምህርት ቤቶች መምህራን እና ሠራተኞች ጋር አብሮ አንድ ላይ ይሠራል። የትምህርት ቤቶች የጽዳት ጠባቂ ሠራተኞች ቡድን (custodial team) በተጨማሪ የትምህርት ቤት ሕንጻ በሚገባ በጥንቃቄ መጽዳቱን እና አይጦችን እና ተባዮችን የመሳሰሉ ጠንቆችን ሊስቡ ከሚችሉ ቆሻሻዎች ጽድቶ የሚገኝ መሆኑን እርግጠኛ ለማድረግ በየቀኑ በቀርጠኛነት ይሠራል።.

ማናቸውም ተባይ፣ በትምህርት ቤት በሚከሰትበት ጊዜ፣ እጅግ ጠንካራ የሆኑ የንጽሕና ጥበቃ እርምጃዎችን እንወስዳለን። በዚህ መሠረት በመጀመሪያ፣ ወያውኑ በፍጥነት ማናቸውም ቀበኛዎች እና ተባዮች በሚከሰቱበት ሰዓት ስለተገኙባቸው ቦታ ወዲያውኑ በዝርዝር ስለ ሁኔታዎቹ መከሰት እናረጋግጣለን። ለምሳሌ፣ ምን እንደታየ፣ መቼ እንደታየ፣ እና በትምህርት ቤት ውስጥ በየትኛው ስፍራ እንደታየ የሚገልጽ ማብራሪያዎችን ያካትታል። ከዚህ በኋላ ይህንን ተከትሎ የትምህርት ቤት ጽዳት ጠባቂዎች ዋና ኃላፊው፣ አካባቢውን በመቃኘት ግምገማ ያካሂድ ኣና አስፈላጊውን ጽዳት እና የአያያዝ ጥበቃ በማከናወን ያጠናቅቃል። አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ አካባቢውን እና ቦታውን በተገቢው መከላከያ መድኃኒቶች መርጨት እንዲችል የተባይ መቆጣጠሪያ አግለግሎት ጊዜ እንዲያዝለት ይደረጋል። በመጨረ ሻም፣ በርካታ የተለያዩ ፀረ ተባይ ድርጅቶች የሚያስፈልጉ ሆኖ ከተገኘ ለተማሪዎች ወላጆች፣ በደብዳቤዎች፣ በኤሜይል፣ አማካኝነት ግኙኝነት ይካሄዳል ወይንም ConnectEd/Robo እንዲሰማራ ይደረጋል።

የተከሰተው ተባይ የአልጋ ትኋን ወይንም ቅማል ሆኖ ከተገኘ የትምህርት ቤቱ የጤና ሞግዚት ተመልክታ በማረጋጋገጥ፣ ታስታውቃለች፣ ችግሩምን ለሚመለከታቸው ተማሪዎች፣ ለወላጆች፣ እና ለመህራን፣ ለሠራተኞች ገለጻ እና ማብራሪያ፣ ቀጥሎም መወሰድ ስለአለባቸው እርምጃዎች እና ስለ አለውም የመከላከያ ዝግጅት ሁኔታ እንዲያውቁ ታደርጋለች። እባክዎን ተማሪዎች፣ ለትኋን እና ለቅማል ተባዮች ከትምህርት ቤት ክልል እንደማይወገዱ ልብ ይበሉ። ትኋኖች በትምህርት ቤት መራባት እና መዛመት እንዲሁም መኖር እንደማይችሉ እባክዎን ልብ ይበሉ።

ከወኪል ድርጅቶች አጋሮቻችን ጋር በመካሄድ ላይ ያለውን ጥረቶቻችንን ስንቀጥል እና የተለመደ የዘወትር አያያዝ እና ንጽሕና ጥበቃችንን በማካሄድ ላይ እያለን የትምህርት ቤቶቻችንን ሕንጻዎች በንጽሕና ለመያዝ እና የደኅንነት ዋስትናቸውን የተጠበቀ ለማድረግ ጠቅላላ የትምህርት ቤት ማኅበረሰብ ከፍተኛ ተግባር ያከናውናል። ቆሻሻ እና የማይፈልግ ምግብ በሥርዓት እንዲወገድ ከማድረግ አንሥቶ እስከ በመመገቢያ አዳራሾች ክልል ምግብ በተወሰነ ደረጃ እንዲቅረብ በማድረግ አንድ ላይ ሁላችንም የተባዮች ሁኔታ እንዲቀንስ ማድረግ እንችላለን። የትምህርት ቤቶቻችን ሕንጻዎች ሁሉ በንጽሕና እንዲጠበቁ እና የደህንነት ዋስትና እንዲኖራቸው ለምታደርጓቸው አስተዋጽዖዎች እናመስገናለን።

ከልባዊ ሠላምታ ጋር፣

Antwan Wilson
ቻንስለር (Chancellor)
ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DC Public Schools)

Greer Johnson Gillis,
ሥራ አስኪያጅ (Director)
የጠቅላላ አገልግሎቶች መምሪያ (Department of General Services)